የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር
Ministry Of Trade & Regional Integration

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር

## የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሰራር የማስፈጸሚያ ማኑዋል

ህዳር 14/2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ


**ክፍል አንድ** ........ 1
1.መግቢያ ........ 1
1.1.አጭር ርዕስ ........ 2
1.3 ዓላማ ........ 4
1.5 የአሰራር ማንዋሉ ዝግጅት አስፈላጊነት እና ጠቀሜታዉ ........ 4
**ክፍል ሁለት** ........ 6
2.1.1 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የቅድመ ዝግጅት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራቶች ........ 6
2.1.2 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የትግበራ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራቶች ........ 6
2.1.3 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የክንውን አፈፃፀምና የሪፖርት ሂደት ........ 8
2.2 አጠቃላይ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወይም የገበያ ኢንስፔክሽን ዋና ዋና ተግባራቶችና የአሰራር ሂደቶችንና ፍሰቶችን የሚያሳይ ቻርት ........ 8
2.2.1 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ የአሰራር ቅደም ተከተል /ሂደት ቻርት መግለጫ ........ 10
**ክፍል ሶስት** ........ 12
3 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አፈፃፀም ላይ ተዋናኝ የሆኑ አካላት ተግባርና ሃላፊነት ........ 12
3.2 የጥራት ማረጋገጫ መሪ ስራ አስፈጻሚ ተግባርና ሃላፊነት ........ 12
3.4 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ኢንስፔክተሮች ተግባርና ሃላፊነት ........ 13
3.5 እርምጃ የሚወሰድባቸው አግባቦች ........ 15
**ክፍል አራት** ........ 16
4. በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ዙሪያ የጥቆማ፣ የቅሬታና አቤቱታ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ........ 16
4.1.2 የጥቆማ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቻርት መግለጫ ........ 17
4.2.2 የቅሬታ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቻርት መግለጫ ........ 19
**ክፍል አምስት** ........ 21
5.1 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች አዘገጃጀት፣ የአያያዝ ቁጥጥር፣ የማፅደቅና የስርጭት ስርዓትን በተመለከተ ........ 21
5.2 የማፅደቅ ስርዓት ........ 21
5.3 የቁጥር አሰጣጥ ስርዓት ........ 21
5.4 የስርጭት ስርዓት ........ 22
5.5 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ማኑዋልና ቼክሊስቶችን ማሻሻያ በተመለከተ ........ 22
**ክፍል ስድስት** ........ 23
6. የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ሰነዶችና ቅፅዎች ........ 23
6.1 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ........ 23
6.2 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ ሰነዶች ........ 23
6.3 አባሪዎች ........ 24
6.4 የማኑዋሉ ማጣቀሻዎች ሰነድ ........ 34
6.5 የአሠራር ማንዋሉ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ ........ 34

# ክፍል አንድ

## 1. መግቢያ

በሀገሪቱ ያለው የንግድ እንቅስቃሴ በየወቅቱ እያደገና እየሰፋ በመምጣቱ የህብረተሰቡን ደህንነትና ጤንነት እንዲሁም የአካባቢን ደህንነት ለመጠበቅ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸውን የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር እንዲያደርግ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት መሠረት የስራ ኃላፊዎች እና ተቆጣጣሪዎች የገበያ ምርት ጥራት ቁጥጥር የሚያካሂዱበትን ወጥ አሠራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በገበያ በመገኘት የጥራት ቁጥጥር የሚካሄድባቸው ምርቶች ላይ የእይታ ኢንስፔክሽን ማከናወን፣ናሙና መውሰድ፣ላቦራቶሪ ማስፈተሽ ፣ የእይታ ኢንስፔክሽን እና የቤተ-ሙከራ ፍተሻ ውጤቶችን መተንተን፣ ማጠናቀር፣በተገኘው የውጤት ትንተና ግኝት መሠረት ከደረጃ በታች የሆኑ ምርቶችን ወደ ገበያ በሚለቁ አካላት ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ፣ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸዉን ለህግ ማቅረብ፣ ማስፈፀም፣መከታተል እና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር በተቀናጀ መልኩ የተጣለበትን ኃላፊነት በመወጣት በገበያ ውስጥ የሚገኙ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን የንግድ ዕቃዉች/ምርቶች/ ጥራታቸውን በዘላቂነት ማስጠበቅ ተገቢ በመሆኑ፤

የገበያ ምርቶች ጥራት የማስጠበቅ ተግባርን ለማከናወን የስራ ክፍሉ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ግልፅነትና ተጠያቂነት በመላበስ የሚሰሩበትና የሚመሩበት ማኑዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ረቂቅ ማንዋሉ ህዳር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ለሚኒስቴሩ ሚኒ ካቢኔ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የተሰጡ ግብአቶችን አካቶ በሥራ ላይ እንዲውል በተሰጠው ውሳኔ መሠረት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይህን "የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሠራር ማስፈጸሚያ ማኑዋል" (Work Procedure Manual) አውጥቷል።

### 1.1. አጭር ርዕስ

ይህ ማኑዋል "የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሠራር የማስፈጸሚያ ማኑዋል (Work Procedure Manual "ቁጥር 02/2015 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 1.2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ የአሰራር ማኑዋል ውስጥ፡-

1. “ሚኒስቴር" እና “ሚኒስትር” ማለት እንደቅደም ተከተሉ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው፤
2. “ኢንስፔክሽን” ማለት የንግድ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ወይም ሂደቶች አስገዳጅነት ካላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚደረግ የዕይታ፣ የመለካት፣ የመመዘን እና በቤተ ሙከራ ፍተሻ የሚከናወን ተግባር ነው፤
3. "ኢንስፔክተር" ማለት ሚኒስቴሩ በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 22 (1) (ቸ) መሠረት አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸው የንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የደረጃውን መስፈርት ስለማሟላታቸው ለመቆጣጠር የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመፈፀም የሚመድበው ባለሙያ ነው፤
4. "የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር" ማለት በገበያ ላይ የሚገኙ ምርቶች በአስገዳጅ ደረጃዎች ላይ የተቀመጡትን የጥራት መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በገበያ ቦታዎች ላይ የሚከናወን የቁጥጥር ተግባር ነው፤
5. “አስገዳጅ ደረጃ” ማለት ምርቶችና አገልግሎቶች የግድ ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የያዘ ደረጃ ነው፤
6. “መስፈርት” ማለት የሕብረተሰቡን ጤና፣ ደህንነትና ጥቅም እና የአካባቢ ደህንነትን ለመጠበቅ ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል የተደነገገ የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ማሟላት ያለባቸው ተፈላጊ ዝርዝር ሁኔታዎች ናቸው፤
7. “የፊዚካል ኢንስፔክሽን” ማለት ምርቶች እና አገልግሎቶች ከወጣላቸው አስገዳጅ የጥራት ደረጃ መስፈርት አንፃር ማሟላትና አለማሟላታቸውን ለማረጋገጥ የሚካሄድ የዕይታና የመለካት ፍተሻ ስራ (Sensory evaluation) ነው፤
8. “የላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት” ማለት የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች የተቀመጠላቸውን ብሄራዊ ድንጋጌዎችንና መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በላቦራቶሪ በመመርመር ውጤቱን የማሳወቅ ሥራ ነው፤
9. “ወካይ ናሙና” ማለት የአንድን የንግድ ዕቃ/ምርት የጥራት ደረጃን ለማረጋገጥ ለዕይታና ለቤተ-ሙከራ ፍተሻ ከገበያ ላይ የሚወሰድ የንግድ ዕቃ/ምርት ዓይነት ነው፤

10. "የቴክኒክ ደንብ" ማለት የንግድ ዕቃዎችን/ምርቶችን ባህሪያትና ከእነርሱ ጋር የተዛመዱ የማምረቻ ዘዴዎችን እንዲሁም አስገዳጅነት ያላቸውን የአስተዳደር ድንጋጌዎች የያዘ ሰነድ ሆኖ መስፈርት ማሟላት አስገዳጅ የሆነበትና በተጨማሪነትም አንድን የንግድ ዕቃ/ምርት ወይም ሂደት በተመለከተ እንደሚኖራቸው አግባብ የቃላቱን ፍቺዎች፣ ምልክቶች፣ የአስተሻሸግ መለያ የማድረግ፣ የአርማ መስፈርቶችን አጠቃሎ የያዘ ደንብ ነው፤
11. "የአስገዳጅ ደረጃ ምልክት" ማለት አንድ የንግድ ዕቃ/ምርት አግባብነት ካለው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ጋር ተስማሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ/ የሚያመለክት የደረጃ ምልክት ነው፤
12. "ተስማሚነት ምዘና" ማለት አንድ የንግድ ዕቃ/ምርት ከወጣለት የጥራት ደረጃ መስፈርት አንፃር ማሟላቱንና አለማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚሰራ የምርመራ ስራ ነው፤
13. "የምርት ጥራት ሰርተፍኬት" ማለት ከተስማሚነት ምዘና በኋላ ለአንድ የንግድ ዕቃ/ምርት ደረጃውን ስለማሟላቱ የሚያረጋግጥ በሶስተኛ ወገን የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤
14. "ሸማች" ማለት የንግድ እቃዎችን ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የሚጠቀም/ የሚገዛ/ የተፈጥሮ ሰው ነው፤
15. "አገልግሎት" ማለት ደመወዝ ወይም የቀን ሙያተኛ ክፍያ ያልሆነ፣ ገቢ የሚያስገኝ ማንኛውም አገልግሎት የመስጠት የንግድ ስራ ወይም ግብዓትን ወደ ውጤት የሚቀይሩ የተቀናጁ ወይም የተጣመሩ ተግባራት ውጤት ነው፤
16. "ችርቻሮ ሻጭ" ማለት የንግድ ዕቃዎችን ከጅምላ ሻጭ ወይም ከአምራች ወይም ከአስመጭ ገዝቶ ለሸማች ወይም ለተጠቃሚ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤
17. "ጅምላ ሻጭ" ማለት የንግድ እቃዎችን ከአምራች ወይም ከአስመጪ ገዝቶ ለቸርቻሪ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው፤
18. "አስመጪ" ማለት የንግድ እቃዎችን በየብስ ወይም በባህር ወይም በአየር ከውጪ ሀገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስመጣ ሰው ነው፤
19. "የንግድ ዕቃዎች" ማለት ገንዘብና ገንዘብነት ካላቸው ሰነዶች በስተቀር ማናቸውም የሚገዙ ወይም የሚሸጡ ወይም የሚከራዩ ወይም በሌላ ሁኔታ በሰዎች መካከል የንግድ ስራ የሚከናወንባቸው የሚንቀሳቀሱ ዕቃዎች ናቸው፤
20. "ተገቢ ያልሆነ የንግድ ሥራ" ማለት ንግድን የሚመለከት የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስ ማንኛውም ድርጊት ነው፤

21. "አስተዳደራዊ እርምጃ" ማለት የንግድ ተቋማት ህግን ተላልፈው ሲገኙ እንደ አስፈላጊነቱ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና አሰራሮችን መሰረት በማድረግ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚወሰድ እርምጃ ነው፤
22. "የንግድ ድርጅት ማገድ" ማለት የንግድ ድርጅቱ በሮችና መስኮቶች ሳይታሸጉ ነጋዴው ሥራውን እንዲያቆም ፈቃዱ ለጊዜው የታገደ መሆኑን በደብዳቤ/በጽሁፍ መግለጽ ነው፤
23. "የንግድ ድርጅት ማሸግ/ መዝጋት" ማለት "የንግድ ሥራው የሚፈጸምበትን መደብር ሥራውን ለማስቆም መስኮቶችንና በሮቹን በባለድርጅቱ እንዲቆለፍ አድርጎ መቆለፉን በማረጋገጥ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ማህተም ባለበት ስለመታሸጉ የሚገልጽ ደብዳቤ በማጣበቂያ በበሩ እና በመስኮቱ መክፈቻ ወይም መገጣጠሚያ ላይ እንደተዘጋ መለጠፍ ነው፤
24. "የንግድ ፍቃድ መሰረዝ" ማለት የንግድ ድርጅቶች/ግለሰብ ነጋዴዎች ባወጡት የንግድ ፍቃድ መሰረት የንግድ ስራቸውን እንዳይሰሩ ያወጡትን የንግድ ፍቃድ የተሰረዘ መሆኑን በደብዳቤ/ በጽሁፍ መግለጽ ነው፤
25. "የንግድ ዕቃ/ምርት ከገበያ መሰብሰብ" ማለት አምራቾች/አስመጪዎች/ የንግድ ዕቃዎቹ/ ምርቶቹ ባለቤት የሆኑ ድርጅቶች ወደ ገበያ የለቀቁትን ወይም ያሰራጩትን የንግድ ዕቃ/ምርት በገበያ ላይ መቆየቱ የህዝብ ጤናና ደህንነት እንዲሁም የንግድ ስርዓቱን ስጋት ላይ የሚጥሉ ሆነው ሲገኙ በድርጅቶቹ አማካኝነት ከገበያ ቦታዎች/ከንግድ ተቋማት ሙሉ በሙሉ የተሰራጩትን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች እንዲሰበሰቡ ማድረግ ነው፤

## 1.3 ዓላማ

በገበያ ላይ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች የወጣላቸውን አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የሕብረተሰቡን ጤና፣ ደህንነት፣ጥቅም እና የአካባቢን ደህንነት ለማስጠበቅ በሚደረገው የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሠራር ሂደትና ፍሰት በግልፅ ማሳየት ነው።

### 1.3.1 ዝርዝር ዓላማዎች

1.3.1.1 የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተቆጣጣሪዎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን በተከተለ የአሰራር ሂደትና ፍሰት መሰረት የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ሥራን እንዲያከናውኑ ማስቻል፣

1.3.1.2 ክፍተቶችን በመለየት አዳዲስ አሰራሮችን ለመተግበርና በቀጣይነት ስራውን ለማሻሻል፤

1.3.1.3 እንደ ስልጠና ሰነድ በመጠቀም ተቆጣጣሪዎችን የክህሎት ክፍተት ለመሙላት፤

## 1.4 የማኑዋሉ የተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ የአሰራር ማኑዋል የተፈፃሚነት ወሰን በገበያ ላይ የሚገኙ አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸው ምርቶች የተቀመጠላቸውን የአስገዳጅ ደረጃ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚከናወን የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ተግባር ላይ ይሆናል፡፡

## 1.5 የአሰራር ማንዋሉ ዝግጅት አስፈላጊነት እና ጠቀሜታዉ

- የተግባር አንድነትን፣ ቅልጥፍናን፣ የሥራ ጥራትን፣ በፈፃሚዉ ዘንድ በራስ መተማመንና የመወሰን ችሎታን ያጐለብታል፣
- የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አፈጻጸም ሂደት ወጥ የሆነ የአሰራርና የቁጥጥር ስርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን ያስችላል፣
- በአሠራር ሂደት የሚስተዋሉ ወጥነት የጐደላቸው አሰራሮችን ለመፍታት ያስችላል፣
- ምቹ የሆነ የጥቆማ አቀራረብ ስርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣
- በአፈፃፀም ወቅት የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን ለመቀበልና ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል

# ክፍል ሁለት

## 2 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሰራር ሂደቶችና ፍሰቶች

### 2.1. የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ዋና ዋና ተግባራቶች እና የአሰራር ሂደቶች

የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር አጠቃላይ የአሰራር ሂደት እንቅስቃሴዎች የቅድመ ዝግጅት ሂደት፣የትግበራ ሂደት፣የክንውን አፈፃፀም/የሪፖርት ሂደት እና የማስተካከያ/እርምጃ የመውሰድና ክትትል የማድረግ ሂደት በሚል በአራት ዋና ዋና የአሰራር ሂደቶች ተከፋፍሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### 2.1.1 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የቅድመ ዝግጅት ሂደት የሚከናወኑ ተግባራቶች

- የመሥሪያ ቤቱን ዓመታዊ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ዕቅድ መሰረት በማድረግ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የሚካሄድባቸውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች፣ የሚገኙበትን የገበያ ቦታ/የንግድ ተቋማት፣ የኢንስፔክሽን ስራው የሚከናወንበትን የጊዜ ሰሌዳና ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን ያካተተ የጥራት የኢንስፔክሽን ዕቅድ/ፕሮግራም ማዘጋጀት፡፡
- ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን (በማኑዋሉ ክፍል አምስት ላይ አስፈላጊ ግብዓቶች በሚለው ሥር በዝርዝር የተጠቀሱትን) ማዘጋጀት/እንዲሟሉ ማድረግ፡፡
- የጥራት ኢንስፔክሽን ስራውን የሚያከናውኑ ኢንስፔክተሮችን በመመደብ ለኢንስፔክሽን ስራ ወደ መስክ ሲወጡ ማንነታቸውን የሚገልፅ የመስሪያ ቤቱን ህጋዊ መታወቂያና ስራውን እንዲያከናውኑ የተፈቀደበትን ደብዳቤ ማዘጋጀትና እንዲይዙ ማድረግ፡፡
- ሌሎች ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ማስታዎሻና ደብዳቤዎችን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ክፍል ማሳወቅ፡፡
- በኢንስፔክሽን ISO/IEC 17020 እና ነባርና አዳዲስ የቴክኒክ ደንቦችን፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች እና አለም አቀፍ ደረጃዎች (ISO/IEC, Codex Alimentarius, ARSO or Reginal Standard) መሰረት ቅጾችን ማዘጋጀት እና ምቹ ማድረግ፡፡

#### 2.1.2 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የትግበራ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራቶች

- በቅድመ ዝግጅት ሂደት በተዘጋጀው የምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወይም የገበያ ኢንስፔክሽን ዕቅድ/ፕሮግራም መሰረት በገበያ ላይ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ጥራትና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን፣ የአገልግሎት ጊዜ ያላለፈባቸዉ መሆናቸውን፣ ማሸጊያቸው ላይ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ

ትክክለኛ የምርት መግለጫ (የተመረቱበት ጊዜ፣ አገልግሎታቸው የሚያበቃበት ጊዜ፣ እንደ አግባቡ የተዘጋጁባቸው ንጥረ ነገሮች ይዘት፣ የተመረቱበት ሃገር፣ የንግድ ዕቃው/ምርት አጠቃቀምና ጥንቃቄ፣ ብሔራዊ የጥራት ደረጃ ምልክትና ሌሎች መሰረታዊ መግለጫዎች) ያላቸዉ መሆኑን እንዲሁም ከሌሎች ባዕድ ከሆኑ ነገሮች ጋር ያልተቀላቀሉና ያልተበላሹ መሆናቸውን በገበያ ቦታዎች /የንግድ ተቋማት በመገኘት የእይታ ኢንስፔክሽ ሪፖርት ማድረጊያ ቅፅ በመጠቀም የገበያ ፊዚካል /ዕይታ ኢንስፔክሽን ሥራ ማካሄድ፣

- የቁጥጥር ስራዎች በሚካሄዱበት ወቅት የአገልግሎት/መጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው፣ ከሌሎች ባዕድ ከሆኑ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉና የተበላሹ እንዲሁም በሰው ጤናና ደህንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የንግድ ዕቃዎች በገበያ ቦታዎች /የንግድ ተቋማት ከተገኙ ህግና ስርዓትን በተከተለ መልኩ የንግድ መደበሩን የማሸግና የታሸገበትን መሰረታዊ ምክንያት ኢንስፔክተሮቹ በቃለ ጉባኤ መልክ ሪፖርት ማቅረብ፣
- ከእይታ ኢንስፔክሽን በተጨማሪ የሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች አስገዳጅ ደረጃው በሚፈቅደው አግባብ በተዘጋጀላቸው የናሙና መውሰጃ ቸክሊስት መሰረት በገበያ ቦታዎች/ የንግድ ተቋማት ላይ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎችን/ምርቶችን ወካይ ናሙና ከገበያ ላይ በግዥ መውሰድ፣ለመስሪያ ቤቱ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ፣እንደገና በመረከቢያ ፎርም ናሙናዎችን የመረከብ ስራ ይሰራል::
- ለማመሳከሪያ (counter sample) ሆነው ከሚቀሩት ውጭ ያሉ ወካይ ናሙናዎችን ማንነታቸውን የሚገልጸውን መግለጫ (labling) በማጥፋት በቀሪውና ለላብራቶሪ ፍተሻ በሚላከው ወካይ ናሙና ላይ ተመሳሳይ መለያ ቁጥር (የሚስጥር ኮድ) በመስጠት የተቀመጠላቸውን አስገዳጅ የጥራት መስፈርት ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ለተስማሚነት ምዘና ለላብራቶሪ ፍተሻ በደብዳቤ መላክና ውጤቱ የሚደርስበትን የቀን ቀጠሮ የመቀበል፣
- የወካይ ናሙናዎችን የላቦራቶሪ ፍተሻ ውጤት /እንደተላከው ናሙና ዓይነት/ በተቀመጠላቸው የፍተሻ ጊዜ መሠረት ከተስማሚነት ምዘና ድርጅቶች ውጤቶችን የመረከብ፣
- በእይታ ኢንስፔክሽን እና በሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የተገኙ የኢንስፔክሽን ስራ ውጤቶችንና መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና የተቀመጠላቸውን አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የማያሟሉ የንግድ ዕቃዎችን/ምርቶችን ወደ ገበያ

ያሰራጩ ድርጅቶችን/አካላትን ለመለየት በግብይት ሰንሰለቱ የተገኙ የንግድ ዕቃዎችን ህጋዊ የሽያጪ ደረሰኞችን መሰረት በማድረግ አስፈላጊውን የማጣራት ስራ በመስራት በቂ ማስረጃና መረጃ የማሰባሰብ ስራ የሚሰራ ይሆናል፣

### 2.1.3 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የክንውን አፈፃፀምና የሪፖርት ሂደት

በእይታ ኢንስፔክሽንና በሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ፍተሻ የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ አጠቃላይ የጥራት ኢንስፔክሽን ሪፖርት ማዘጋጀት ሲሆን በአፈፃፀም ሪፖርቱ ላይ ሊካተቱ የሚገባቸው ነጥቦች:-

- የአምራች /አስመጪ/ አከፋፋይ/ ቸርቻሪ ድርጅት ስምና አድራሻ፣
- ወካይ ናሙናው የተወሰደበት የንግድ ዕቃ/ምርት ዓይነት፣ የተገዛበት ቀንና የንግድ ዕቃው/ ምርቱ የተመረተበት ሀገር፣
- በእይታ ኢንስፔክሽን ስራ የተገኙ የኢንስፔክሽን ውጤቶች ከተለያዩ የንግድ ህግ ማዕቀፎች እንዲሁም የሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የሚያስፈልጋቸው አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ የወጣላቸውን የንግድ ዕቃ ወካይ ናሙና በላቦራቶሪ ፍተሻ የተገኙ ውጤቶች ከአስገዳጅ ደረጃው/የጥራት መስፈርት አንፃር በመተንተን የመነሻ የውሳኔ ሀሳብ፣
- የገበያ ኢንስፔክሽኑን ያካሄዱት ባለሙያዎች ስም፣ ፊርማና ቀን፣

## 2.2 አጠቃላይ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ወይም የገበያ ኢንስፔክሽን ዋና ዋና ተግባራቶችና የአሰራር ሂደቶችንና ፍሰቶችን የሚያሳይ ቻርት

| ግብዓት | የስራ ሂደት | ውጤት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1. የመሥሪያ ቤቱን ዓመታዊ ዕቅድ፣ግብዓትና የሰው ሀይል | የቁጥጥር ዕቅድ ማዘጋጀት | የተዘጋጀ የገበያ ኢንስፔክሽን ሥራ ዕቅድ /ፕሮግራም | ዲስክ ኃላፊው/ የስራ ሂደት መሪ/ ስራ አስፈጻሚው |
| 2. የተዘጋጀ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ሥራ ዕቅድ | የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ዝርዝር ዕቅድ | የተዘጋጀ የገበያ ኢንስፔክሽን ሥራ ዝርዝር ዕቅድ/ፕሮግራም | መሪ ኢንስፔክተርና የኢንስፔክሽን አባላት |
| 3. የተዘጋጀ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ሥራ ዝርዝር ዕቅድ | የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ግብዓት ዝግጅት<br>አዎ | ለገበያ ኢንስፔክሽን ስራ የተዘጋጀ ዝርዝር ግብዓት | ዲስክ ኃላፊው/ የስራ ሂደት መሪ/ ስራ አስፈጻሚው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4. ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ የተዘጋጀ ዝርዝር ግብዓት | የገበያ ቦታ/የንግድ ተቋማት መገኘትና የቁጥጥር ስራ መስራት | የእይታ ኢንስፔክሽ ውጤትና ለላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የተወሰደ አስገዳጅ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ወካይ ናሙናና የተገዙበት የግዢ ደረሰኝ | ኢንስፔክተሮች |
| 5. የእይታ ኢንስፔክሽ ውጤትና ለላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የተወሰደ አስገዳጅ ደረጃ ያላቸው ወካይ ናሙናና የተገዙበት የግዢ ደረሰኝ | ለወካይ ናሙና ኮድ በመስጠት በሶስተኛ ወገን ላብራቶሪ ማስፈተሽ | አስገዳጅ የኢትዮጲያ ደረጃ ያላቸው የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ወካይ ናሙና የላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የምርመራ ውጤት | መሪ ኢንስፔክተርና የኢንስፔክሽን አባላት፣ ተስማሚነት ምዘና ድርጅቶች |
| 6. የኢንስፔክሽን (የፊዚካልና ላብራቶሪ) የምርመራ ውጤት | የእይታ ኢንስፔክሽን እና የወካይ ናሙናው የተስማሚነት ምዘና ውጤት ማጠናቀርና | የተጠናቀረና የተተነተነ የገበያ ኢንስፔክሽን ስራ ሪፖርት | ኢንስፔክተር |
| 7. የተጠናቀረና የተተነተነ የገበያ ኢንስፔክሽን ስራ ሪፖርት | ስጋት ?<br>የለም → ሪፖርት<br>አለ | ጥራት፣ ደህንነትና አስገዳጅ የጥራት ደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ወካይ ናሙናዎች ዝርዝር ሪፖርት | የኢንስፔክሽን ቡድን |
| 8. ጥራት፣ ደህንነትና አስገዳጅ የጥራት ደረጃ መስፈርት የማያሟሉ ወካይ ናሙናዎች ዝርዝር ሪፖርት | የጥራት ጉድለት የታየባቸውን የገበያ ምርቶች ወደ ገበያ ያሰራጩ አካላትን ለመለየት መረጃና ማስረጃ የማሰባሰብ ስራ | የንግድ ዕቃውን/ የምርቱን ምንጭ የሚገልፅ መረጃና ማስረጃ ሪፖርት | የኢንስፔክሽን ቡድን |
| 9. የንግድ ዕቃውን /የምርቱን ምንጭ የሚገልፅ መረጃና ማስረጃ ሪፖርት | የእርምት እርምጃ ምንነት?<br>አለ → አስተዳደራዊ እርምጃ<br>የለም | የተደረጃ ለህጋዊ እርምጃ ክስ የሚረዱ ማስረጃና መረጃዎች | ዲስክ ኃላፊው/ የስራ ሂደት መሪ/ ስራ አስፈጻሚው |
| 10. የተደረጃ ለህጋዊ እርምጃ ክስ የሚረዱ ማስረጃና መረጃዎች | ክስ መመስረት | የተመሰረተ ክስ | ፖሊስ/ አቃቢ ህግ |
| 11. የተመሰረተ ክስ | የህጋዊ እርምጃ ስምምነት? | የተወሰነ ህጋዊ እርምጃ | የሚመለከተው ፍርድ ቤት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12. የተወሰነ ህጋዊ እርምጃ | የአፈፃፀም ክትትል | በተወሰዱት ህጋዊ እርምጃ መሰረት የተስተካከሉ ጉድለቶች | ዲስክ ኃላፊው/ የስራ ሂደት መሪ/ ስራ አስፈጻሚው |

## 2.2.1 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ የአሰራር ቅደም ተከተል /ሂደት ቻርት መግለጫ

1. የዴስክ ኃላፊው/የመሪ ስራ አስፈጻሚው የመሥሪያ ቤቱን ዓመታዊ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ዕቅድ፣ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ የግብዓት አቅርቦትና የሰው ሀይል መሰረት በማድረግ የገበያ ኢንስፔክሽን ዕቅድ/ፕሮግራም የሚያዘጋጅ ይሆናል፡፡
2. ኢንስፔክተሮቹ ከዴስክ ኃላፊው/ከመሪ ስራ አስፈጻሚው የወረደላቸውን የገበያ ኢንስፔክሽን ዕቅድ/ፕሮግራም መሰረት በማድረግ የገበያ ኢንስፔክሽን የሚካሄድባቸውን የንግድ ዕቃዎች/ ምርቶች፣ የሚገኙበትን የገበያ ቦታ/የንግድ ተቋማት የኢንስፔክሽን ስራው የሚከናወንበትን የጊዜ ሰሌዳና ሌሎች ከስራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን ያካተተ ዝርዝር የኢንስፔክሽን ዕቅድ/ፕሮግራም የሚያዘጋጁ ይሆናል፡፡
3. በዝርዝር የቁጥጥር ዕቅድ መሠረት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በዴስክ ኃላፊው/ በመሪ ስራ አስፈጻሚው አማካኝነት እንዲሟሉ ይደረጋል፣ በኢንስፔክተሮች በኩል ደግሞ አስፈላጊ ቼክ ሊስቶች የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡
4. ዝርዝር የቁጥጥር ዕቅድን እና የቀረቡ ግብዓቶችን መሰረት በማድረግ በገበያ ላይ የሚገኙ የንግድ ዕቃዎቹ/ምርቶች የተቀመጠላቸውን የአስገዳጅ ደረጃ መስፈርት አሟልተው ስለመገኘታቸው በገበያ በመገኘት የእይታ ኢንስፔክሽ ሪፖርት ማድረጊያ ቅፅ በመጠቀም የገበያ ፊዚካል/ዕይታ ኢንስፔክሽን ሥራ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ከእይታ ኢንስፔክሽን በተጨማሪ አስገዳጅ ደረጃው በሚፈቅደው አግባብ በተዘጋጀላቸው የናሙና መውሰጃ ቸክሊስት መሰረት የንግድ ዕቃዎችን/ምርቶችን ወካይ ናሙና ከገበያ ላይ በግዥ መውሰድ፣ ለመስሪያ ቤቱ ንብረት ክፍል ገቢ ማድረግ፣ እንደገና በመረከቢያ ፎርም ናሙናዎችን የመረከብ ስራ ይሰራል፡፡
5. ወካይ ናሙናው ከተወሰደ በኋላ ኢንስፔክተሮቹ ናሙናው የተወሰደበትን መደብር /ድርጅት የንግድ ፍቃድ ሥም፣ የተወሰደው የንግድ ዕቃ/የምርት ዓይነት፣ የተወሰደው የናሙና ብዛት፣ የተመረተበትና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ጊዜ፣ የምርቱ አያያዝ ሁኔታ፣ የንግድ ምልክቱ፣ ምርቱ የተሰራበት ግብዓት እና ሌሎች ለዕይታ ኢንስፔክሽን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመሙላት ለማመሳከሪያ (counter sample) ሆነው ከሚቀሩት ውጭ ያሉ ወካይ ናሙናዎችን ማንነታቸውን

የሚገልጸውን መግለጫ (labling) በማጥፋት በቀሪውና ለላብራቶሪ ፍተሻ በሚላከው ወካይ ናሙና ላይ ተመሳሳይ መለያ ቁጥር (የሚስጥር ኮድ) በመስጠት የተቀመጠላቸውን አስገዳጅ የጥራት መስፈርት ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ለተስማሚነት ምዘና ለላብራቶሪ ፍተሻ በደብዳቤ መላክና የፍተሻ ውጤቱን በሚደርስበት የቀን ቀጠሮ መቀበል፡፡

6. ኢንስፔክተሮቹ በእይታ ኢንስፔክሽን እና በሶስተኛ ወገን የላብራቶሪ ፍተሻ ማረጋገጫ የተገኙ የኢንስፔክሽን ስራ ውጤቶችንና መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ዝርዝር ሪፖርት ለዴስክ ኃላፊው የማቅረብ ስራ ይካሄዳል፡፡
7. ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና የተቀመጠላቸውን አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት የማያማሉ የንግድ ዕቃዎችን /ምርቶችን በመለየት እንዲሁም ስጋት የማያስከትሉትን እንደማያስከትሉ እና በቀጣይ የማጣራት ስራ የሚያስፈልጋቸውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች የሚገልፅ ዝርዝር ሪፖርት ለዴስክ ኃላፊው/ ለመሪ ስራ አስፈጻሚው የሚቀርብ ይሆናል፡፡
8. በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ኢንስፔክተሮቹ ተጨማሪ የማጣራት (Traceablity) ሥራ የሚሠራባቸውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ገበያ ቦታዎች /የንግድ ተቋማት ላይ መጀመሪያ የገዙበትን ደረሰኝ በመያዝ ናሙናውን ከገዙበት ነጋዴ ምርቶቹ የተገዙበትን የጅምላ አከፋፋዩን ህጋዊ የሽያጭ ደረሰኝ ቅጅ በመውሰድ የንግድ ዕቃውን/ የምርቱን ምንጭ (አምራች/ አስመጪ) የመለየት ሥራ የሚሰራ ሲሆን ምንጩ አስመጪ ሆኖ ከተገኘ የንግድ ዕቃውን/ምርቱን ከየት ሀገር እንዳስመጣው፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዴት እንደገባ፣ ምርቱ ሲገባ ጥራቱን አሟልቶ የገባ ስለመሆኑ የፍተሻ ውጤትና እንዲገባ ፍቃድ የተሰጠበት ወረቀት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያሳዩ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በመሰብሰብና በማጠናቀር እንዲሁም በመተንተን እና ሙያዊ የመነሻ የውሳኔ ሐሳብ የያዘ ሪፖርት በቡድን መሪው በኩል ለዳይሬክተሩ የሚቀርብ ይሆናል፡፡
9. የዴስክ ኃላፊው/ ከመሪ ስራ አስፈጻሚው/ ጋር በጋራ በመሆን የቀረበውን ሪፖርት በመገምገም የታየውን ግድፈት ከሚያመጣው ጉዳት ጋር በማመዛዘን በአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 22 (1) (ቸ)፣ በንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 አንቀጽ 29(1) 'ሀ' የተቀመጠውን የእርምጃ ዓይነት መሰረት በማድረግ መወሰድ ያለባቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች የሚወስድ ይሆናል፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ከአቅም በላይ የሚሆኑ ውሳኔዎችን ለዘርፉ በማቅረብ ያስወስናል፣ ዘርፉ እንዲወሰዱ ያስቀመጣቸውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል ይከታተላል፣ የሚወሰደው አሥተዳደራዊ እርምጃ በቂ ካልሆነና በቀጥታ ጉዳዩ በህግ እንዲታይ ከተወሰነ ዳይሬክቶሬቱ ለህጋዊ እርምጃ የሚረዱ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን በማጠናቀር ለህግ ክፍል በማስታዎሻ የሚልክ ይሆናል፡፡
10. የዴስክ ኃላፊው/ መሪ ስራ አስፈጻሚው የተወሰኑ ውሳኔዎችን ተፈጻሚነት ይከታተላል:

ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

# ክፍል ሶስት

## 3 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አፈፃፀም ላይ ተዋናኝ የሆኑ አካላት ተግባርና ሃላፊነት

የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ሥራ ላይ ከዝግጅት ጀምሮ እስከ እርምጃ አወሳሰድና ክትትል ሥራ ድረስ ባሉ ሂደቶች ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ በተለያዩ ደረጃ እና የስልጣን ተዋረድ ላይ ያሉ አካላት የየራሳቸው የሆነ ተግባር እና ኃላፊነት አላቸው፡፡ ስለሆነም በእያንዳንዱ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ትግበራ ሂደት ውስጥ ያላቸውን ተግባርና ኃላፊነት በግልፅ ማስቀመጥ ሥራውን በግልጸኝነት እና በተጠያቂነት ማከናወን የሚያስችል በመሆኑ በየደረጃው ያሉ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

### 3.1 የጥራት መሠረተ ልማት ማረጋገጫ ዘርፍ እና የከፍተኛ ማኔጅመንት ተግባርና ሃላፊነት

1. የታየውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ጥራት፣ ደህንነትና አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት ያለማሟላት ጉድለት አስመልክቶ ከስራ ክፍሉ አቅም በላይ የሚሆኑ የአስተዳደራዊ እርምጃዎች የውሳኔ ሐሳቦችን እንደ አስፈላጊነቱ አስተያየትና ማስተካከያ በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤፣
2. የታየውን የምርት ጥራት ጉድለት አስመልክቶ ምርቱ ከገበያ የሚሰበሰብበትንና በሚዲያ የሚገለፅበትን የእርምጃ የውሳኔ ሀሳብ ይሰጣል፤፤

### 3.2 የጥራት ማረጋገጫ መሪ ስራ አስፈጻሚ ተግባርና ሃላፊነት

የጥራት ማረጋገጫ መሪ ስራ አስፈጻሚ ኃላፊነትና ተግባር በJEG በተሰጠው ደረጃ የስራ ዝርዝር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚ በታች ያሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፤

1. የታየውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት ያለማሟላት ጉድለት አስመልክቶ ከዴስክ ኃላፊው/አስተባባሪው የሚቀርቡ የአስተዳደራዊ እርምጃዎች የውሳኔ ሐሳቦችን ያፀድቃል፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስተያየትና ማስተካከያ በማድረግ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤
2. የታየውን የምርት ጥራት ጉድለት አስመልክቶ ምርቱ ከገበያ ስለሚሰበሰብበት እና በሚዲያ ስለሚገለፅበት ሁኔታ ዴስኩ ባቀረበው የእርምጃ ማስታወሻ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

3. ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድበት አግባብ ሲኖር በቀረበለት የውሳኔ መነሻ ሐሳብ መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ የሕግ ምክር በመጠየቅና እንደ ግብአት በመጠቀም የመጨረሻ ውሳኔ በመስጠት ወደ ህግ ክፍል ውሳኔውን ይመራል፤
4. በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ዓመታዊ የገበያ ምርት ጥራት ቁጥጥር እቅድ ያዘጋጃል፣
5. ለገበያ ኢንስፔክሽን ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ ያደርጋል፣
6. የንግድ ዕቃ/ምርት ጥራትን አስመልክቶ ውስጣዊ እና ውጫዊ ባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፣
7. ባለሙያዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ዕድሉን በማመቻቸት የባለሙያዎችን አቅም ይገነባል፤

### 3.3 የዴስክ ኃላፊ ተግባርና ሃላፊነት

የዴስክ ኃላፊ ኃላፊነትና ተግባር በJEG በተሰጠው ደረጃ የስራ ዝርዝር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚ በታች ያሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፤

1. በምርት ጥራት ዙሪያ ከጥራት ማረጋገጫ ስራ አስፈጻሚ የወረደለትን ዓመታዊ የገበያ ኢንስፔክሽን ስራ እቅድ መሰረት በማድረግ በየግማሽ ዓመቱ እየከፋፈለ በማቀድ ለኢንስፔክተሮች ያስተላልፋል፤
2. በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የሚከናወኑ ስራዎችን በሪፖርት መልክ ለመሪ ስራ አስፈጻሚው ያቀርባል፣ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የአስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል ፤ያስፈጽማል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
3. የታየውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርት ያለማሟላት ጉድለት አስመልክቶ ሊወሰዱ የሚገባቸውን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በመለየት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል፤
4. ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ሥራ የሚያስፈልጉ የግብአት ፍላጎት ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲሟሉ ያደርጋል፣
5. የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ኢንስፔክተሮችን በማስተባበር ለገበያ ኢንስፔክሽን ሥራ የሚያገለግል ቢጋር እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ስራውን በቅርብ ያስተባብራል፣ ይገመግማል፣ ይከታተላል፣
6. እንደአ ስፍላጊነቱ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የኢንስፔክተሮችን የስራ ምድባ ሊለዉጥ ይችላል፡፡

## 3.4 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ኢንስፔክተሮች ተግባርና ሃላፊነት

የዴስክ ኃላፊ ኃላፊነትና ተግባር በJEG በተሰጠው ደረጃ የስራ ዝርዝር ወሰን እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚ በታች ያሉትን ተግባራት ያከናውናሉ: በአንድ የንግድ ተቋም ተገኝተው የሚቆጣጠሩ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ኢንስፔክተሮች ከ3/ሶስት/ ማነስም ሆነ መብለጥ የሌለባቸው ሲሆን፡-

1. በማንኛዉም ሰዓት ለኢንስፔክሽን ስራ በሚሄዱበት የገበያ ቦታ/የንግድ ተቋማት የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ሰራተኛ መሆናቸውን የሚገልፅ የተቆጣጣሪነት መታወቂያና ከተቋሙ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ እንዲሰሩ ፍቃድ የተሰጠበትን ህጋዊ ደብዳቤ በማሳየት የመጡበትን ተግባር በመግለጽ ህግና ስርዓትን በተከተለ መልኩ አስፈላጊውን የኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ስራዎችን የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፣
2. በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ የተገኙ ውጤቶችን በመተንተንና በማደራጀት እንዲሁም መወሰድ ያለበትን ሙያዊ የመነሻ የውሳኔ ሃሳብ የያዘ ሪፖርት ለዴስክ ኃላፊው የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው፣
3. ኢንስፔክተሮች ነጋዴዉን ማስተማር፣ መደገፍ፣ ህገ-ወጦች ላይ መደለያ መጠየቅ፣ መቀበል ፈፅሞ የተከለከለ ሲሆን የደንብ ጥሰት ፈጽሞ የተገኘን ነጋዴ አይቶ ማለፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ህገ-ወጥነትን ማስፋፋት ተደርጎ ይወሰዳል፣
4. በንግድ ዕቃዎች/ምርቶች የጥራት ጉድለትን አስመልክቶ የጉዳዩ ባለቤት ላይ የታዩበትን የጥራት ችግሮች የደንብ ጥሰት ሳያዛቡ በቃለ ጉባኤ አስደግፎ ሪፖርት የማቅረብና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እዉነታዉን ማእከል ያደረገ የምስክርነት ቃል በፍ/ቤት ተገኝቶ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፣
5. ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን መጠየቅና በአግባቡ መጠቀም ይችላሉ፣ ሰነዶችን /ቅፃ ቅፆችን/፣ ቢጋሮችን ያዘጋጃሉ፣
6. የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራዎች በሚካሄዱበት ወቅት የአገልግሎት/መጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው፣ ከሌሎች ባዕድ ከሆኑ ነገሮች ጋር የተቀላቀሉና የተበላሹ እንዲሁም በሕዝብ ጤናና ደህንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ የንግድ ዕቃዎች በገበያ ቦታዎች /የንግድ ተቋማት ከተገኙ ህግና ስርዓትን በተከተለ መልኩ የንግድ መደበሩን ማሸግና የታሸገበትን መሰረታዊ ምክንያቶች በቃለ ጉባኤ መልክ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፣
7. በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ የተገኙ መረጃዎችን ሚስጥርነታቸው በተጠበቀ መልኩ መያዝ ይኖርባቸዋል፣

8. ኢንስፔክተሮች ለወሰዱት ናሙና ሀላፊነት መውሰድ አለባቸው፡፡

9. ስራቸውን ከማንኛውም ወገን ጥቅምና አድልዎ በፀዳ መልኩ ማከናወን አለባቸው፣

## 3.5 እርምጃ የሚወሰድባቸው አግባቦች

የአስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014፣ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጽ 29(1) 'ሀ፤ ለ እና ሐ" እንዲሁም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ህጎችን የጣሰ ወይም የተላለፈ ወይም በተቀመጠው የደረጃ መስፈርቶች የጥራት ደረጃዎችን ያላሟላ ድርጅት ላይ የመነሻ ውሳኔ ሀሳብ ያቀርባሉ፣

## 3.6 የማመሳከሪያ ቀሪ (counter sample) ናሙናዎች የአወጋገድ ስርዓት

ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥርና ለላብራቶሪ ፍተሻ ከገበያ ላይ የተወሰዱ የንግድ እቃዎች/ምርቶች በማመሳከሪያነት (counter sample) የሚቀመጡ ወካይ ናሙናዎች የሚደረገው ጠቅላላ የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ከተጠናቀቀ በኋላ የሚወገዱበት አግባብ:-

1. ሶሥት (3) ወር በላይ በመጋዘን ለማመሳከሪያነት (counter sample) የተቀመጡ ወካይ ናሙናዎች ለላብራቶሪ ፍተሻ አገልግሎት ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ በንግድ ዕቃዎቹ/ምርቶች ላይ የሚደረገው የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥርን ስራ እና ውሳኔ ያላገኙ ቢሆኑም የሚወገዱ ይሆናል፡፡
2. ሶስት ወር ያልሞላቸው ነገር ግን የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራቸው እና የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ የንግድ እቃዎች/ምርቶች የግድ ሶስት ወር እስኪሞላቸው ሳይጠበቅ መወገድ ይችላሉ፡፡
3. የንግድ እቃዎች/ምርቶች የአወጋገድ አግባብ እንደየንግድ እቃው/ምርቶች የሚለያይ ሲሆን በዚህም መሰረት:-

- ምግብና ምግብ ነክ እንዲሁም ከሰው ቆዳ ጋር ቀጥታ ንክኪ ያላቸው (የንፅህና መስጫ እቃዎች/ምርቶች) የንግድ እቃዎች/ምርቶች በሚደረግላቸው ፍተሻ ደረጃቸውን ያሟሉ ቢሆንም በመጋዘን የቆይታ ወቅት የጥራት ችግር ሊከሰት ስለሚችል ሰው እንዳይጠቀምባቸው ግልጽና ተጠያቂነት ባለው መልኩ የአካባቢን ደህንነት በማይጎዳ አግባብ የኢንስፔክሽን ባለሙያዎችና የመስሪያ ቤቱ የንብረት ማስወገድ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት በቃለ ጉባኤ የሚወገዱ ይሆናል፡፡
- ከምግብና ምግብ ነክ እንዲሁም ከሰው ቆዳ ጋር ንክኪ ካላቸው (የንፅኅና መስጫ እቃዎች) ውጭ ያሉ የንግድ እቃዎች/ምርቶች በሚደረግላቸው ፍተሻ ደረጃቸውን ያሟሉ ከሆኑ አገልግሎት ላይ ቢውሉ ጉዳት ስለማያደርሱ በመንግስት የጨረታ ስርዓት መሰረት በጨረታ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡
- በየትኛውም አግባብ የጥራት ጉድለት የተገኘባቸው ማንኛውም የንግድ እቃ/ ምርቶች ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ግልጽና ተጠያቂነት ባለው አካባቢን በማይጎዳ አግባብ የኢንስፔክሽን ባለሙያዎችና የመስሪያ ቤቱ የንብረት ማስወገድ የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት በቃለ ጉባኤ የሚወገዱ ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

## 4. በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ዙሪያ የጥቆማ፣ የቅሬታና አቤቱታ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት

የገበያ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ሥራዎችን ወጥነት ባለው መልኩ በማከናወን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ጥራትን በማረጋገጥ የህዝብን ጤና፣ ደህንነትና ጥቅም ከማስጠበቅ እንዲሁም ፍትሃዊና ተወዳዳሪ የንግድ ስርዓ ከመዘርጋት አንፃር የጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ አቀባበል ስርዓት ዘርግቶ መስራት አስፈላጊ ነው።

### 4.1 የጥቆማ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት

1. ማንኛውም አካል በንግድ ዕቃዎች/ምርቶች ጥራት፣ ደህንነትና አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃ መስፈርቶች ዙሪያና ሌሎች ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለመሥሪያ ቤቱ የሚያቀርበውን ጥቆማ የጥራት ማረጋገጫ ዲፓርትመት ወይም የገበያና ፋብሪካ ምርቶች ጥራት ማረጋገጥ ዴስክ በደብዳቤ፣ በጥቆማ መቀበያ ፎርም፣ በስልክ እና ሌሎች አመች በሆኑ መንገዶች በመጠቀም ይቀበላል።
2. የህብረተሰብን ጤና፣ ደህንነትና ጥቅም የሚጎዱ፣ የአካባቢን ደህንነት ለስጋት የሚጥሉ እንዲሁም የንግድ ውድድሩን የሚያዛቡ ህገወጥ የንግድ አሰራርን ለመከታተል ያመች ዘንድ የጥቆማ ስልኮችን በየንግድ መደብሩ በመለጠፍ፣ በማስታወቅ የጥቆማ ስርዓት በመዘርጋት ጥቆማዎችን በአግባቡ የመቀበል ስራ ይሰራል።
3. ከህብረተሰቡ በሚደርሱ ጥቆማዎች መሰረት ጥቆማ በቀረበበት የንግድ ተቋም/ የንግድ እቃ ላይ ፈጣን ድንገተኛ የማጥራት ስራዎችን በማካሄድ የህብረተሰቡን ጤንነትና ደህንነት የሚያዉክ መሆኑ ከተረጋገጠ ቅሬታ የቀረበበት ተቋም ግድፈቶቹ ተገልጸዉለት በ10 ቀናት ዉስጥ ግድፈቶቹን እስከሚያስተካክል ድረስ አግባብ ባለው የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት የንግድ ስራ ፈቃዱ ይታገዳል፣ በታገደ የንግድ ፈቃድ ሲሰራ የተገኘ የንግድ ድርጅት ታሽጎ ይቆያል፣ ተደጋጋሚ ጥፋት ላይ ተሰማርቶ የተገኘ የንግድ ድርጅት የንግድ ስራ ፈቃዱ ይሰረዛል፣ መረጃም እንዲደራጅበት ተደርጎ ክስ ይመሰረትበታል።

4. እንደ አስፈላጊነቱ ጥቆማው በቀረበበት የንግድ ተቋም/የንግድ ዕቃ ላይ በማጣራት የተገኙ ጉድለቶችንና ለጉድለቱ የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለጠቋሚዉ አካልና የሚዲያ አካላቶችን በመጠቀም ህብረተሰቡ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡

### 4.1.1 የጥቆማ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ የአሰራር ቻርት

| ግብዓት | የስራ ሂደት | ዉጤት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1. ጥቆማ | ጥቆማን መቀበል ↓ | የተመዘገበ ጥቆማ /ቅሬታ | የስራ ክፍሉ ኃላፊ |
| 2. የተመዘገበ /የቀረበ ጥቆማ | የቀረበውን ጥቆማ መገምገም/ማጣራት ↓ | የተገመገመ /የተጣራ ጥቆማ | የኢንስፔክሽን ኢንስፔክተሮች |
| 3. የተገመገመ /የተጣራ ጥቆማ | የጥቆማው አግባብነት? — የለውም → ለጥቆማ አቅራቢው ማሳወቅ; አለው ↓ | ለቀረበው ጥቆማ የውሳኔ/እርምጃ ማስታዎሻ/ ቃለ-ጉባኤ | የስራ ክፍሉ ኃለፊ፣ |
| 4. ለቀረበው ጥቆማ የውሳኔ/እርምጃ ማስታዎሻ/ቃለ-ጉባኤ | የአስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ↓ | የተወሰደ የአስተዳደራዊ እርምጃ ዓይነት | የስራ ክፍሉ ኃለፊ |
| 5. የተወሰደ የአስተዳደራዊ እርምጃ ዓይነት | የተወሰደውን እርምጃ/ምላሽ ማሳወቅና ጉድለቱ መስተካከሉን መከታተል | የተሰጠ ምላሽ ሪከርድ | የስራ ክፍሉ ኃለፊ፣ |

### 4.1.2 የጥቆማ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቻርት መግለጫ

1. ጥቆማን በቃል፣ በደብዳቤ፣ በጥቆማ መቀበያ ቅጽ፣ በስልክ፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመጠቀም መቀበል ይቻላል፡፡ በማንኛውም መልኩ የቀረቡት ጥቆማዎች ተመዝግበው ተያያዥ መረጃዎች

ካሉ በማያያዝ የራሳቸው መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው የሚያዙ ይሆናል። በተሰጣቸው መለያ ቁጥር መሰረት በስራ ክፍሉ ኃላፊ በኩል በፍጥነት እንዲጣሩ ይደረጋል።

2. የዴስክ ኃላፊው/ መሪ ስራ አስፈጻሚው ከኢንስፔክተሮች ጋር በመሆን የቀረቡለትን የጥቆማ መረጃዎች በፍጥነት እንደ አስፈላጊነቱ ጥቆማው የቀረበበት የንግድ ተቋም ድረስ በመሄድ በትክክል የማጣራት ስራ ይሰራል።

3. የተጣራው ቅሬታ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ጥቆማ አቅራቢው በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል። በሌላ በኩል ቅሬታው ተቀባይነት እንዳለው ከተረጋገጠ የዴስክ ኃላፊው/መሪ ስራ አስፈጻሚው ከቡድኑ ኢንስፔክተሮች ጋር በመሆን በማጣራት ወቅት የተገኘውን የኢንስፔክሽን ውጤት መሰረት በማድረግ መወሰድ ያለበትን የእርምት የእርምጃ ዓይነት በማስታዎሻ /በቃለ-ጉባኤ ለስራ ክፍሉ ኃላፊ/መሪ ስራ አስፈጻሚው የሚያቀርብ ይሆናል። ነገር ግን በማጣራት ወቅት ጊዜ የማይሰጥ ህገወጥ ተግባር ሆኖ ከተገኘ እና የንግድ ተቋሙን የሚያሳሽግ ድርጊት ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ በቃል ለዴስክ ኃላፊው/መሪ ስራ አስፈጻሚው በማሳወቅ የማሸግ ስራ በመስራት በቃለ-ጉባኤ የታሸገበትን ምክንያት የሚያቀርብ ይሆናል።

4. መሪ ስራ አስፈጻሚው በዴስክ ኃላፊው በኩል የቀረበለትን የውሳኔ ሐሳብ መነሻ በማድረግ ለቀረበው ጥቆማ ወቅታዊና ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወስድ ይሆናል።

5. ጥቆማ በቀረበበት የንግድ ድርጅት ላይ የተወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ ለጠቋሚው አካልና ለህብረተሰቡ እንደአስፈላጊነቱ በቃል ወይም በጽሁፍ ወይም ሚዲያዎችን በመጠቀም የማሳወቅ ስራ የሚሰራ ይሆናል።

### 4.2 የቅሬታ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ

1. የስራ ክፍሉ ኃላፊ/አስተባባሪ ማንኛውም አካል በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራዎችና በሚወሰዱ የማስተካከያ አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተመለከተ የሚያቀርበውን ቅሬታ ጉዳዩ በተፈጸመ በ10 (አስር) የስራ ቀናት ውስጥ መቅረቡን በማረጋገጥ በቃል፣ በፅሁፍ ወይም ለቅሬታ መቀበያ ተብሎ በተዘጋጀው የቅሬታ መቀበያ ቅጽ በማስሞላት ቅሬታውን ይቀበላል።
2. የስራ ክፍሉ ኃላፊ/አስተባባሪው ለቀረበው ቅሬታ በ10 የስራ ቀናት ውስጥ በማጣራት በፅሁፍ ምላሽ የሚሰጥ ሆኖ ሌሎች ከቅሬታው ጋር በተያያዘ የቤተ-ሙከራ ፍተሻ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ ለቅሬታው የሚሰጠው ምላሽ ለፍተሻ የሚወስደውን ጊዜ ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል።

3. በቅሬታው ላይ የተሰጠው ውሳኔ በቂ አይደለም ብሎ ያመነ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባስቀመጠው የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መሠረት የማቅረብና ምላሽ የማግኘት መብት አለው፡፡

### 4.2.1 የቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን የሚያሳይ የአሰራር ቻርት

| ግብዓት | የስራ ሂደት | ዉጤት | ኃላፊነት |
|---|---|---|---|
| 1. የቅሬታ ማመልከቻ | ቅሬታን መመዝገብ | የተመዘገበ ቅሬታ | የስራ ክፍሉ ኃላፊ/አስተባባሪው |
| 2. የተመዘገበ ቅሬታ | የቀረበውን ቅሬታ መገምገም/ማጣራት | የተገመገመ /የተጣራ ቅሬታ | መሪ ኢንስፔክተሮች |
| 3. የተገመገመ /የተጣራ ቅሬታ | የቅሬታው አግባብነት? — የለውም → ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ; አለው ↓ | ለቀረበው ቅሬታ የውሳኔ ሀሳብ ማስታዎሻ/ ቃለ-ጉባኤ | መሪ ኢንስፔክተሮች |
| 4. ለቀረበው ቅሬታ የውሳኔ ሀሳብ ማስታዎሻ/ ቃለ-ጉባኤ | ለቅሬታው ተመጣጣኝ መፍትሄና ምላሽ | ውሳኔውን ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅና ሪከርድ ማድረግ | የስራ ክፍሉ/እንደ አስፈላጊነቱ ዘርፉ/ሚኒስትሩ |

### 4.2.2 የቅሬታ አቀባበልና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ቻርት መግለጫ

1. የክፍሉ ኃላፊ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በቃል፣ በደብዳቤ፤ በቅሬታ መቀበያ ቅጽ፣ በስልክ፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በመጠቀም መቀበል ይችላል፡፡ በማንኛውም መልኩ የቀረበ ቅሬታ ተመዝግቦ ተያያዥ መረጃዎች ካሉ በማያያዝ የራሱ መለያ ቁጥር ተሰጥቶት የሚያዝ ይሆናል፡፡ በተሰጠው መለያ ቁጥር መሰረት በዳይሬክቶሬቱ/የስራ ክፍሉ በኩል በፍጥነት እንዲጣሩ ይደረጋሉ፡፡

2. የስራ ክፍሉ ኃላፊ/አስተባባሪ የቀረቡለትን የጥቆማና ቅሬታ መረጃዎች በትክክል የማጣራት ስራ ይሰራል፡፡
3. የቀረበው ቅሬታ ተገምግሞ/ተጣርቶ ቅሬታው ተቀባይነት የሌለው መሆኑ ከተረጋገጠ ቅሬታ አቅራቢው ስለዚህ ሁኔታ በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩል ቅሬታው ተቀባይነት እንዳለው ከተረጋገጠ አግባብነት ያለው ኢንስፔክተር የቅሬታ አቅራቢውን ጉዳይ በመመርመር ተወስኖ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ችግሩን በማጣራት የውሳኔ ሐሳብ ማስታወሻ ቃለ ጉባኤ በመሪ ኢንስፔክተሩ አማካኝነት ለስራ ክፍሉ ኃላፊ/አስተባባሪ የሚቀርብ ይሆናል፡፡
4. የስራ ክፍሉ ኃላፊ/አስተባባሪው በኩል የቀረበለትን የመነሻ የውሳኔ ሐሳብ መነሻ በማድረግ ለቀረበው ቅሬታ ተመጣጣኝ መፍትሄ ወይም ምላሽ በጽሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው አካል ምላሽ ይሰጣል፡፡
5. እንደአስፈላጊነቱ በዳይሬክቶሬቱ በኩል የተሠጠው የቅሬታ ምላሽ አጥጋቢ ካልሆነ ቅሬታ ያቀረበው አካል ጉዳዩን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባስቀመጠው የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መሠረት የማቅረብና ምላሽ የማግኘት ሂደቱ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

# ክፍል አምስት

## 5.1 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች አዘገጃጀት፣ የአያያዝ ቁጥጥር፣ የማፅደቅና የስርጭት ስርዓትን በተመለከተ

ወጥነት ባለው አግባብ ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን (የአሰራር ማኑዋሎችንና ቼክ ሊስቶችን) ለማዘጋጀት፣ ለማፅደቅ፣ለማሰራጨት/ጥቅም ላይ ለማዋል/ቁጥጥር ለማድረግና በሪከርድነት ለማስቀመጥ፣ ለማሻሻልና እንደአስፈላጊነቱ ለማስወገድ ሲባል የሰነድ አያያዝ ስርዓት ማዕቀፍ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም መሰረት፡-

## 5.1 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አዘገጃጀት በተመለከተ

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በገበያ ላይ የንግድ ዕቃ/ የምርት ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለማከናወን የተለያዩ ቼክ ሊስቶችና ፎርማቶችን ማዘጋጀት የሚጠይቅ በመሆኑ እነዚህ ሰነዶች ከንግድ ዕቃ/ምርት ጥራት ቁጥጥር ጋር የተያያዙ ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራትን፣ አስገዳጅ የኢትዮጵያ ደረጃዎችን፣ የንግድ ህግን፣ የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅን፣ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አዋጅን እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ህጎች እንዲሁም የአሰራር ስርዓቶችን በግብዓትነት በመጠቀም የሚዘጋጁ ይሆናል፡፡

## 5.2 የማፅደቅ ስርዓት

ሰነዶቹ ለአገልግሎት ከመዋላቸው በፊት ብቁ ስለመሆናቸው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ይፀድቃሉ፡፡ እነዚህ ሰነዶች እንደአስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ግምገማ በማድረግ በማሻሻል ሰነዱ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ሁሉም ሠራተኞች እንዲያውቋቸው የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 5.3 የቁጥር አሰጣጥ ስርዓት

የሰነዶች ቁጥር የሚደረገው በፊደል ቅደም ተከተል ልዩ ቁጥር (MFPQA/Type/xxx) በመስጠት ይሆናል፡፡

በዚህም መሠረት፡-

- MFPQA -የሚወክለው የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር Market and Factory Quality Assurance ነው፡፡

- Type-ጥቅም ላይ የሚውለውን ሰነድ ዓይነት መግለጫ ሲሆን (F) ለቅጾች ወይም ፎርሞች (Forms) የሆኑ ሰነዶችን ለመግለጽ (R) ደግሞ ሪከርድ (Record) የሚደረግባቸው ሰነዶችን ለመግለጽ ነው፡፡
- Xxx- ሰነዶችን በቅደም ተከተል ለመግለጽ የሚቀመጡ ቁጥሮችን ይወክላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሰነድ ቁጥር፣ የሥርጭት ቁጥር፣ የክለሳ ቁጥርና የገጽ ቁጥሮች እያንዳንዱ ሰነድ ራስጌ ላይ ይቀመጣል፡፡ ጥቅም ላይ የማይውሉት ሰነዶች ከአገልግሎት መስጫ ቦታዎች መወገድ አለባቸው፡፡

### 5.4 የስርጭት ስርዓት

የጸደቁ ሰነዶች ለአፈጻጸምና ለማጣቀሻ ለኢንስፔክሽን ሥራ ለሚያስፈልጋቸው ሠራተኞች በተሰጣቸው መለያ የሰነድ ቁጥር መስረት የሚሰራጩ ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ሰነዶች በሚፈለጉበት ወቅት ተደራሽ መሆን መቻል አለባቸው፡፡

## 5.5 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ማኑዋልና ቼክሊስቶችን ማሻሻያ በተመለከተ

ይህን የአሰራር (ማኑዋልና ቼክ ሊስቶችን የማስተዳደር፣ የመገምገምና የማሻሻል ባለቤትነት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሲሆን ሰነዶቹ ጥቅም ላይ ሲውሉ ስራው ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖዎች፣ ውጤቶች እና በሀገሪቱ ያሉትን ተጨባጭ ሁኔታዎች ታሳቢ በማድረግ ይሆናል፡፡ ለማንዋሉ ዝግጅት አስፈላጊ የሆኑ ማጣቀሻዎች፤ አዋጆች፤ አስገዳጅ ደረጃዎች እና ሌሎች ከሥራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ለውጥ ሲኖር እንዲሁም ከባለ ድርሻ አካላት የሚመጡ አስተያየቶችና ግብረ መልሶች ማንዋሉ እንዲሻሻል ሊያስገድዱ ስለሚችሉ ማንዋሉ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ማሻሻያ የሚደረግበት ይሆናል፡፡

# ክፍል ስድስት

## 6 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ ሰነዶችና ቅፅዎች

### 6.1 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች

1. ለኢንስፔክተሮች የሚያስፈልግ ደረጃውን የጠበቀ የደህንነት መገልገያ ቁሳቁስ፡-
    - የደህንነት ጫማና ጋወን
    - የንፅህና መጠበቂያ ሳሙና፣
    - የእጅ ጓንት፣ ጭንብልና ጎግል መነፀር፣
    - የድንገተኛ ህክምና መስጫ ሙሉ መሳሪያ /first aid tool kits)
2. ለወካይ ናሙና መያዣና ዝግጅት የሚያገለግሉ
    - ፕላስቲክ ባግና አይስ ቦክስ
    - ሌብል ማድረጊያ ስቲከርና ፕላስተር፣ ማርከር፣ አልኮል/ቲነር፣
    - የብረት መቁረጫ መጋዝና ፒንሳ፣
    - ዲጅታል ሚዛን፣ ዲጂታል ካሜራ፣ ካሊፐር፣ ሜትር፣ መቀስ፣
3. ደረጃውን የጠበቀ ሽልፍና ፍሪጅ ያለው መጋዝን፣
4. ትራንስፖርት፣ የወካይ ናሙናና የጉልበት ሰራተኛ ክፍያ

### 6.2 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር አስፈላጊ የሆኑ ህጋዊ ሰነዶች

- የኢትዮጵያ አስገዳጅ ደረጃ ሰነዶች፣ የቴክኒክ ደንቦች፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች፣ አለም አቀፍ ደረጃዎች (ISO/IEC, Codex Alimentarius, ARSO or Reginal Standard)
- አስገዳጅ ደረጃ የወጣላቸውን የንግድ ዕቃዎች/ምርቶች/አገልግሎቶች ለመቆጣጠር የሚያስችል አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች፣

## 6.3 አባሪዎች

### 6.2.1 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ቅጽ (market Product Quality Controll Checklist)

#### 6.2.1.1 የወካይ ናሙና ግዥና የእይታ እይታ ኢንስፔክሽ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | የድርጅት /አምራች/ አስመጪ/ አከፋፋይ ስም፡-_______________ | | |
| 2 | አድራሻ፡-<br>ክልል /ከተማ አስተዳደር፡-_______________<br>ዞን/ክ. ከተማ/ _______________ ወረዳ፡ _______________<br>ስልክቁጥር፡ _______________ሞባይል፡_______________ ቲን ቁ._______________ | | |
| 3 | ወካይ ናሙናው የተወሰደበት የንግድ ዕቃ ምርት ዓይነት፡-_______________ | | |
| 4 | የናሙና አወሳሰድ ዘዴ፡ | | |
| 5 | የተወሰደው የናሙና ብዛት ቁጥር እና መጠን፡ | | |
| 6 | ናሙናው የተገዛበት ቀን፡ | | |
| 7 | ወካይ ናሙናው ላይ የተካሄደው የዕይታ /እይታ ኢንስፔክሽ መረጃ፡- | | |
| ተ.ቁ | የንግድ ዕቃው /ምርቱ ማሸጊያ ላይ ሊገለፁ የሚገቡ መግለጫዎች | በእይታ ኢንስፔክሽ የንግድ ዕቃው/ምርቱ ማሸጊያ ላይ በዕይታ የተገኙ መግለጫዎች | ምርመራ |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| 9 | ተጨማሪ አስተያየት/ ውሳኔ ፡_______________<br>_______________<br>_______________ | | |
| 10 | በወካይ ናሙናዎቹ ላይ የእይታ ኢንስፔክሽን ያካሄዱ ባለሙያዎች ስም እና ፊርማ<br>ስም ፊርማ<br>ሀ/ _______________<br>ለ/ _______________<br>ሐ/ _______________<br>ቀን_______________ | | |

### 6.2.1.2 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አሰራር አስፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ መገልገያ ቅጾች

#### 6.2.2.1 የወካይ ናሙና መመዝገቢያና መለያ ሰነድ ቁጥር (Lab.request Log book) መግለጫ ቅጽ

| ተ.ቁ | የሚላከውና ሙና ኮድ | ማጣቀሻ ቁጥር | የናሙናው ዓይነት | የናሙና መጠን | ፍተሻ የሚደረግበት ደረጃ | ናሙናው የተወሰደበት ቀን | ፍተሻ የሚካሄደበት መስፈርት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

### 6.2.1.3 የወካይ ናሙና ሙሉ መረጃ መመዝገቢያ ቅጽ

| ተ.ቁ | ናሙናው የተወሰደበት ቀን | ማጣቀሻ ቁጥር | ናሙናው የተወሰደበት የንግድ ስም | የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር | አድራሻ | | | የኢንስፔክሽን ስራውን ያከናወኑ ባለሙያዎች ስም | ከገበያ የተወሰደው ናሙና | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ክ/ከተማ | ወረዳ | ስ.ቁጥር | | አይነት | መጠን | የተመረተበት አገር | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |

## 6.2.1.4 የላብራቶሪ ናሙና ማስተላለፊያ ቅጽ

| ተ.ቁ | የሚላከው ናሙና ስም | ናሙናው የተላከበት ቀን | የሚላከው ናሙና መጠን | ናሙናውን የተቀበለው ሰው | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ስም | ፊርማ | ቀን | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 6.2.1.5 ለገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ | | | |
| | ናሙናው የተወሰደበት ነጋዴ ስም | አድራሻ፡-<br>ክልል/ከተማ፡...........ዞን/ክ.<br>ከተማ/..............ወረዳ፡........ስልክቁጥር፡.....................ሞባይል፡................<br>ቲንቁ...... | | |
| | የአከፋፋዩ ስም፡ | አድራሻ፡-<br>ክልል/ከተማ፡.................ዞን/ክ.<br>ከተማ/...........ወረዳ፡...........ስልክቁጥር፡..............ሞባይል፡............ቲንቁ......<br>........ | | |
| | የአምራቹ/አስመጪ ስም፡ | አድራሻ፡-<br>ክልል/ከተማ፡.................ዞን/ክ. ከተማ/...........ወረዳ፡...........ስልክቁጥር፡......<br>ሞባይል፡............ቲንቁ............. | | |
| 2 | ወካይናሙናው የተወሰደበት ምርት ዓይነት | | | |
| 3 | የናሙና አወሳሰድ ዘዴ፡ | | | |
| 4 | የተወሰደው የናሙና ብዛትቁጥር እና መጠን፡ | | | |
| 5 | ናሙናው የተገዛበት ቀን፡ | | | |
| 6 | ምርመራ፡<br>የተቀመጠለትን አስገዳጅ የምርት ጥራት ደረጃ አላሟል ☐ | አሟልቷል ☐ | | |
| | 6.1. ካላሟላ፡- | | | |
| | የወካይናሙናው ምርት ስም | የተፈተሸበት የደረጃ መስፈርት | ከእይታ ምርመራ አስገዳጅ ደረጃ አንፃር ያላሟለው መስፈርት | ከቤተ-ሙከራ ምርመራ አስገዳጅ ደረጃ አንፃር ያላሟለው መስፈርት |
| | | | | |
| | | | | |
| | | | | |

**6.2 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ኢንስፔክተሮች አስተያየትና የመነሻ የውሳኔ ሀሳብ፡**

ስምና ፊርማ

ሀ/ ______________________

ለ/ ______________________

ሐ/ ______________________

ቀን፡______________

6.3. የገበያና ፋብሪካ ምርቶች ጥራት ማረጋገጥ ዴስክ ኃላፊ የመነሻ ውሳኔ ሀሳብ፡

ስም፡______________________ ፊርማ ________ ቀን________

6.4. የጥራት ማረጋገጫ መሪ ስራ አስጻሚ የውሳኔ ሀሳብ፡

ስም፡______________________ ፊርማ ________ ቀን________

6.2.1.6 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን የማስተናገጃ ቅፅ/ Market Surveillance Complain Form

1

ጥቆማውን ያቀረበው ድርጅት /ግለሰብ/

1.1. ስም:..........................................................................................................

1.2. አድራሻ ፡ ከተማ ................................ክ/ከተማ ..........................ወረዳ ........................ቀ.ቁ

1.3. ጥቆማው የቀረበበት ቀን:..............................................................................

1.4. የጥቆማው ይዘት:....................................................................................................

1.4.1. የየንግድ ዕቃ/ምርት ጥራት ችግር ከሆን፡

1. ጥቆማው የቀረበበት የንግድ ዕቃ/ምርት ዓይነት:..............................................................................

2. የሀገር ውስጥ ምርት ☐ የገቢ ምርት ☐ አይታወቅም ☐
~~አይታወቅም~~

3. የንግድ ዕቃ/ምርቱ ተሰራጭቶ የሚገኝበት የገበያ ቦታ:..............................................................................

4. የዕቃ/ምርቱ አምራች ወይም አስመጪ ድርጅት ስም:..............................................................................

   አድራሻ፡ ከተማ .............................ክ/ከተማ .......................... ወረዳ .................... ቀ.ቁ .....

5. ጥቆማ ከተደረገበት ድርጅት ጋር ያላቸው ግንኙነት ካለ:..............................................................................

ጥቆማውን ያቀረበው ድርጅት /ግለሰብ/ ፊርማ: ................................ ቀን: ..................................

**ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**

1. በቀረበው ጥቆማ ላይ አስፈላጊው ምርመራ/ማጣራት ተደርጎበት በኢንስፔክተሮች የተሰጠ አስተያየት:
..............................................................................
..............................................................................
..............................................................................

የገመገመው የኢንስፔክተር ስም: .........................ፊርማ: ................................. ቀን: .........................
............................ፊርማ: ..........................ቀን: ................................
............................ፊርማ: ..........................ቀን: .................

2. በዴስክ ኃላፊ የተሰጠ የውሳኔ ሀሳብ:
..............................................................................

የገመገመው በዴስክ ኃላፊ ስም : ............................ፊርማ: .....................................ቀን:

3. በመሪ ስራ አስጻሚ በኩል የተሰጠ ውሳኔ:
..............................................................................

የገመገመው የመሪ ስራ አስጻሚ ስም: ............................ፊርማ: .....................................ቀን:

6.2.1.7 የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ስራ ቅሬታዎች ማስተናገጃ ቅፅ /Market Surveillance Complain Form

1

**ቅሬታውን ያቀረበው ድርጅት /ግለሰብ/**

1.5. ስም:

.................................................................................................................

1.6. አድራሻ : ከተማ .................ክ/ከተማ .................ወረዳ ...............ቤ.ቁ ...............

1.7. ቅሬታው የቀረበበት ቀን:...........................................................................................

1.8. የቅሬታው ይዘት:

.....................................................................................................................

ቅሬታውን ያቀረበው ድርጅት /ግለሰብ/ ፊርማ: .......................... ቀን: ....................................

**ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**

4. በቀረበው ቅሬታ ላይ አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎበት በኢንስፔክተሮች የተሰጠ አስተያየት:

.....................................................................................................................

.....................................................................................................................

የገመገመው የኢንስፔክተር ስም: ....................ፊርማ: ..........................ቀን: ........................

..................................ፊርማ: ......................................ቀን: ...........

..................................ፊርማ: ......................................ቀን: ..............

5. በዴስክ ኃላፊ የተሰጠ የውሳኔ ሀሳብ:

.....................................................................................................................

.....................................................................................................................

.....................................................................................................................

የገመገመው ዴስክ ኃላፊ ስም: ......................................... ፊርማ: ................................................ ቀን: .......................................................

6. በመሪ ስራ አስጻሚ በኩል የተሰጠ ውሳኔ:

.....................................................................................................................

.....................................................................................................................

.....................................................................................................................

የገመገመው የመሪ ስራ አስጻሚ ስም: ......................................... ፊርማ: ................................................ ቀን: .......................................................

## *6.2.1.8 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የንግድ ዕቃዎ/ምርት የጥራት ጉድለት የተገኘባቸው የንግድ ድርጅቶች ግዴታ መግቢያ ፎርም*

1. ጥፋት የተገኘበት የንግድ ድርጅቱ ስም ____________________
2. የንግድ አድራሻ ከተማ አስተዳደር/ክልል ---------------- ክፍለ ከተማ---------------- ወረዳ-------------የቤት ቁ. ---------------ስል.ቁ. -------የንግድ ምዝገባ ቁጥር --------------የንግድ ፈቃድ ቁጥር ----------------------------------- እኔ በስሜ ከላይ በተጠቀሰው የንግድ ድርጅት በገበያ ኢንስፔክሽን የንግድ ድርጅቴን ድረስ መጥተው በኢንስፔክሽን ስራ ፡

1. ____________________ጥፋት ስለተገኘብኝ ይህ የፈፀምኩት ስህተት መሆኑን የተገነዘብኩ ስለሆነ ----------------- ቀን ውስጥ አስተካክዬ ሪፖርት ባላደርግና ባላስተካክል አዋጅ ቁጥር 1263/2014፣በንግድ ወድድርና ሸማቶች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ 980/2008 አንቀጽ 29(1) 'ሀ፤ ለ እና ሐ" መሠረት እርምጃ ቢወስድብኝ የማልቃወም መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

2. ግዴታ የገባው ነጋዴ ስም/ተወካይ --------------ፊርማ-----------------ቀን--------------
3. ግዴታውን ያስፈረመው የሥራ ኃላፊ--------------- ፊርማ-----------------ቀን-------------

**ማሳሰቢያ-፣**

ይህ ፎርም በሁለት ኮፒ ተዘጋጅቶ አንዱ ለነጋዴው ሁለተኛው ኮፒ በመስሪያ ቤቱ ለስራ ክፍሉ ፋይል ተደርጎ ይቀመጣል፡፡

6.2.1.9 በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር አጠቃላይ የሰነድ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ/ Market Surveillance master document control record

| ተ.ቁ | የሰነዱ/ቅፁ ስም- | ጥቅም ላይ የዋለበት ቀን | የሰነዱ ዓይነት | የስርጭት ቁጥር | የገፅ ብዛት | የክለሳ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የገበያ ኢንስፔክሽን አጠቃላይ የሰነድ መቆጣጠሪያና መመዝገቢያ | 02-02-2009 | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 2. | የገበያ ኢንስፔክሽን የአሰራር ማኑዋል | ›› | Procedure (P) | 01 | | 02 |
| 3. | የወካይ ናሙና ግዥና የእይታ እይታ ኢንስፔክሽ መመዝገቢያና ሪፖርት ማቅረቢያ | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 4. | የወካይ ናሙና ሙሉ መረጃ መመዝገቢያ | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 5. | የወካይ ናሙና መመዝገቢያና መለያ ሰነድ ቁጥር (Lab.request Log book) መግለጫ | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 6. | የላብራቶሪ ናሙና ማስረከቢያ ቅፅ | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 7. | የገበያ ኢንስፔክሽን ስራ ሪፖርት ማቅረቢያ | ›› | Record (R) | 01 | 02 | 02 |
| 8. | በገበያ ኢንስፔክሽን ስራ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን የማስተናገጃ | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 9. | በገበያ ኢንስፔክሽን ስራ የሚቀርቡ ቅሬታዎች የማስተናገጃ | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 10 | በገበያ ኢንስፔክሽን የንግድ ዕቃዎ/ምርት የጥራት ጉድለት የተገኘባቸው የንግድ ድርጅቶች ግዴታ መግቢያ ፎርም | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |
| 11 | ጉድለት በተገኘበት የንግድ ተቋም ላይ የማሸጊያ ፎርም | ›› | Record (R) | 01 | 01 | 02 |

## 6.2.1.10. ጉድለት በተገኘበት የንግድ ተቋም ላይ የማሸጊያ ፎርም

<u>የኢፌዲሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር</u>

የታሸገበት ቀን----------------

በ______________________________________________________________________________ ምክንያት

# ታ ሽ ጓ ል!!

| <u>የኢንስፔክተሩ ስም</u> | <u>የስራ ድርሻ</u> | <u>ፊርማ</u> | <u>የታዛቢዎች ሙሉ ስም</u> | <u>ፊርማ</u> |
|---|---|---|---|---|
| 1.________ | ________ | | ________ | - |
| 2.________ | ________ | | ________ | - |
| 3.________ | ________ | | ________ | - |

## 6.4 የማኑዋሉ ማጣቀሻዎች ሰነድ

| ይህን ማኑዋል ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ የዋሉ ማጣቀሻ ሰነዶች | |
|---|---|
| የሰነድ ቁጥር | የሰነድ ርዕስ |
| ISO/IEC17000:2020 | Conformity assessment – Vocabulary and general principles. |
| ISO/IEC17020:2012 | General criteria for the operation of various types of bodies performing inspection. |
| ISO/Casco guide | Principles and practices in product regulation and market surveillance. ISO Oct. 2012 |
| አዋጅ 1263/2014 | የኢፌዲሪ አስፈፃሚ አካላትን አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 |
| አዋጅ ቁጥር 980/2008 | የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 አንቀጥ 29(1) 29(1) 'ሀ ፣ለ እና ሐ" |
| አዋጅቁጥር 813/2006 | የንግድ አሠራርና ሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 |
| ድረጃዎች | የቴክኒክ ደንቦችን፣የኢትዮጵያ ደረጃዎች እና አለም አቀፍ ድረጃዎች (ISO/IEC, Codex Alimentarius, ARSO or Reginal Standard) |

## 6.5 የአሠራር ማንዋሉ ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ የአሠራር ማኑዋል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፀደቀበት ከህዳር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር 14/2015 ዓ.ም

ገ/መስቀል ጫላ መኮንን አለሜ ሚኒስትር ዴኤታ

........................................

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር Ministry of Trade and Regional Integration

## የውስጥ ማስታወሻ

## Interofice Memo

**ለ፡ ክቡር የጥራት መሠረተ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ**

**ከ፡ ሕግ አገልግሎት ስራ አስፈጻሚ**

**ታህሳስ 12 ቀን 2015 ዓ.ም**

**ጉዳዩ፡- የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሠራር የማስፈጸሚያ ማኑዋል** (Work Procedure Manual "**ቁጥር** 02/2015**ን ይመለከታል**

የገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሠራር የማስፈጸሚያ ማኑዋል (Work Procedure Manual "ቁጥር 02/2015 ህዳር 14 ቀን 2015 ለሚኒስቴር መ/ቤታችን ሚኒ ካቢኔ ስብሰባ ቀርቦ ውይይት የተካሄደበት ሲሆን በውይይቱ የተሰጡ ግብአቶች በሥራ ክፍሉ በኩል እንዲካተቱ ተደርጎ በሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ ከታየ በኋላ በሥራ ላይ እንዲውል ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ ይታወሳል፡፡

የጥራት መሠረተ ልማት ሥራ አስፈጻሚም ማንዋሉን በተሰጡት ግብአቶች መሠረት አዳብሮ ለሕግ አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ በኢሜል ልኮልናል፡፡

በዚህም መሠረት ማንዋሉን ተመልክተን ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ክለሳዎች ያደረግን መሆኑን እየገለጽን በዚሁ መሠረት በቀጣይ ምንም የሀሳብ ወይም የይዘት ለውጥ ሳይደረግበት አስፈላጊ ከሆነ የፎርማት ወይም የኤዲቶሪያል ማሻሻያ ብቻ በማድረግ ማንዋሉ በሚኒ ካቢኔ ታይቶ ከግብአቶች ጋር ከፀደቀበት ከህዳር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡

1. በማንዋሉ መግቢያ የመጨረሻ አንቀጽ ላይ ረቂቅ ማንዋሉ ህዳር 14 ቀን 2015 ዓ.ም ለሚኒ ካቢኔ ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ የተሰጡ ግብአቶችን አካቶ በሥራ ላይ እንዲውል በተሰጠው ውሳኔ መሠረት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ይህን "የገበያ

ምርቶች ጥራት ቁጥጥር የአሠራር ማስፈጸሚያ ማኑዋል" (Work Procedure Manual) ማውጣቱን የሚገልጽ የመደምደሚያ አርፍተ ነገር ተጨምሯል፡፡

2. በማንዋሉ ተራ ቁጥር 1.1 አጭር ርዕስ ላይ "2014 ዓ.ም" የሚለው 2015 በሚል ክለሳ ተደርጎበታል፡፡

3. በትርጉም ክፍል ተራ ቁጥር 3 ላይ ኢኒስፔክተር የሚለው ቃል ሲተረጎም የክልል ንግድ ቢሮዎችን ለማመልከት "አግባብ ያለው አካል" የሚል ያካተተ ሲሆን የክልል ንግድ ቢሮዎች አስፈላጊ መሆኑን ካመኑበት ማንዋሉን ወስደው በራሳቸው አውድ ሊያወጡትና ተግባራዊ ሊያደርጉት ይችላሉ እንጂ ማንዋሉ በእነርሱም ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን በሚጠቁም ሁኔታ ሊዘጋጅ ስለማይገባና የአንድ ማንዋል ተፈጻሚነት ከአንድ መ/ቤት ውስጥም ቢሆን በተወሰነ የሥራ ክፍል በመሆኑ "አግባብ ያለው አካል" የሚለው ቃል ቀሪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ "………ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅና ማንዋል መሠረት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመፈጸም … … …" የሚለው በአስፈጻሚ አካላት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 22 (1) (ቸ) ላይ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመፈጸም መሆኑን በግልጽ በሚያመላክት ሁኔታ ተከልሏል፡፡

4. በትርጉም ክፍል ተራ ቁጥር 18 ላይ አስመጪ የሚለው ቃል ሲተረጎም "የሚያስመጣ ነው" የሚለው "የሚያስመጣ ሰው ነው" በሚል ተከልሏል፡፡

5. በትርጉም ክፍል ተራ ቁጥር 6፣ 7፣ 8፣ 19፣ 22፣ 23 እና 24 "ማለት" የሚለው ቃል በመደምደሚያው ላይ በድጋሚ መጻፉ አላስፈላጊ ድግግሞሽ ስለሆነ እንዲወጣ ተደርጎ ተከልሏል፡፡

6. በገጽ 14 በተራ ቁጥር 3.2 ስር የጥራት መሠረተ ልማት ማረጋገጫ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት ሲዘረዘር በተራ ቁጥር 3 ላይ "እንደ አስፈላጊነቱ የሕግ ምክር በመጠየቅና እንደ ግብአት በመጠቀም" የሚል ሀረግ ተጨምሯል፡፡

7. በገጽ 18 ክፍል 4 ርዕስ "በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ሥራ ዙሪያ የጥቆማ፣ የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት" የሚለው በተለይም አቀራረብ የሚለው ተገልጋዮችን የሚመለከት በመሆኑ በቀጥታ የሚኒስቴር መ/ቤቱን አሠራር እንዲመለከት ለማድረግ በተለይ "አቀራረብ" የሚለው ቃል "አቀባበል" በሚል ተከልሏል፡፡ በዚህም መሠረት አጠቃላይ የክፍል 4 ይዘት ተገልጋዮች እንዴት ጥቆማና ቅሬታ እንደሚያቀርቡ ከመግለጽ ይልቅ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ጥቆማ፣ ቅሬታና አቤቱታ እንዴት እንደሚቀበሉ በሚገልጽ መልክ ተከልሏል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮችን የሚጠቅሰው ሀረግ ከላይ በተራ ቁጥር 2 ላይ በተሰጠው አስተያየት መሠረት እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

8. በገጽ 21 4.2 የቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ በሚለው ተራ ቁጥር 3 በቅሬታው ላይ የተሰጠው ውሳኔ በቂ አይደለም ብሎ ያመነ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ለዘርፉ ብሎም ለሚኒስትሩ ያቀርባል የሚለው ሁሉንም በየወቅቱ የሚኖሩ የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓቶችን እንዲያካትት "ሚኒስቴሩ በዘረጋው የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓት መሠረት ያቀርባል" በሚል ተከልሷል፡፡
9. በገጽ 23 ተራ ቁጥር 4.3 ስለቅሬታ አቀራረብና ውሳኔ አሰጣጥ የሚለው የሀሳቡ ይዘት በቀዳሚው 4.2.2 4 ስር የተካተተ በመሆኑ 4 ለሁለት ተከፍሎ 4 እና 5 ሆኖ ሀሳቡን እንዲያካትት በማድረግ 4.3 ቀሪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡
10. በገጽ 23 ተራ ቁጥር 5.1 ላይ ለገበያ ምርቶች ቁጥጥር ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች አዘገጃጀት፣ የአያያዝ ቁጥጥር፣ የማጽደቅና የስርጭት ሥርዓትን በተመለከተ በሚለው ስር ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተሰጠው አስተያየት መሠረት ክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮችን የሚጠቅሰው ሀረግ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
11. በገጽ 24 ተራ ቁጥር 5.3 ላይ "የቁጥጥር ሥርዓት" የሚለው ርዕስ ከአጠቃላይ ይዘቱ በመነሳት "የቁጥር አሰጣጥ ሥርዓት" በሚል ተከልሷል፡፡
12. በገጽ 25 ተራ ቁጥር 5.5 ላይ በገበያ ምርቶች ጥራት ቁጥጥር ማንዋልና ቸክሊስቶች ማሻሻያን በተመለከተ በሚለው ርዕስ ስር ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተሰጠው አስተያየት መሠረት ክልሎችንና የከተማ አስተዳደሮችን የሚጠቅሰው ሀረግ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡
13. በማንዋሉ በስተመጨረሻ ላይ ማንዋሉ የጸደቀበትና በሥራ ላይ የዋለበት ቀን ሲቀመጥ ለሚኒ ካቢኔ ቀርቦ ውይይት የተደረገበትና የተሰጡ ግብዓቶች ተካትተውበት በሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነበት ማለትም ስብሰባው የተካሄደበት ቀን ህዳር 14 2015 እንዲሆን ተደርጓል፡፡